# ለምን አይበላ?

ከመዝገበ ባየህ

ነፍሱን ካኮሰሰ፣ ለሥጋው ሲያደላ፣
ይሰለቀጥ እንጂ ምነው አይበላ!?
ይበላዋል እንጂ ምነው አይበላ
አህያ አለው አይደል ከበግና ፍየል የበለጠ ስጋ?
ወያኔ ሰው በላ ወገን አጥፊ ባንዳ፣
ሀገሩን ለመሸጥ፣ የማያወላዳ፣
ምኑ ያስገርማል!
ምኑ ያስደንቃል!
ትርፍን ቢያሰባስብ ከአህያ ቆዳ!

ሽሮ ሰላሳ ብር ኪሎ ስጋ ሰባ
ወገን በፍርሃት ተቀምጦ ከሰባ
ሀገር ሲቸብቸብ ላረብ፣ ህንድ፣ ለቻይና፣
ሀይ የሚል ከጠፋ፣ መልካ ሆኖ ወና፣
ቻይናም ስግብግብ ነው ወርቅ ዋጭ አህያ
ወያኔም ሆዳም ነው ሁሉን ለገበያ ::
ስርዓቱ ሰው በላ ስንት ዜጋ የፈጀ
በደምና ሥጋ በቅሎ የደረጀ
በጎሳ ፍረጃ፣ ስንቱ ተገደለ፣
ኢትዮጵያዊነትም፣ ወንጀል ነው ተባለ።
ሀገርን ለማጥፋት፣ ምለው ተማምለው፣
ወቀሳን ከስንም ሲጨማምር ውሎ
እየተሻሻጠ፣ ሰውን እየሸጠ
ህዝቡን በጭቆናው እንዳልቀጠቀጠ
ላገር ተቆርቋሪ ሀሳቢ ነኝ ብሎ
አህያ ለዕድገት ብሎ መጣ እነሆ።

ጊዜም አለፈና ዘረኛው አገዛዝ ሰው መብላት ሰልችቶት

መሸንሸን መሸጡ የሀገርን መረት ለባዕድ ቱጃሮች ከቶ አልበቃ ብሎት

አህያን ቢያሻሽጥ ምኑ ያስገርማል

ወያኔ ሰው በላ  ሀገር ሕዝብን ሸጧል ።

ይበላዋል እንጂ ምነው አይበላ

ወያኔ አረመኔ እንኳንስ አህያ አይምር የሰው ስጋ!

የሚያስማማ እናቱን የሚሸጥ ደላላ!

ዛፍና አርቃዩን (ሸንበቆ)፣ መሸጥ የለመደ

ያውም ጫካ ሳለ

ዛሬ ሀገር ቢሸጥ ለምን አስገረመ?

ሺዎችን ጨፍጭፎ የሰው ደም አፍሶ

በአፈና ድልዳል ስርዓቱን ገንብቶ

ሀያ ዓመት የበላን ሀያ ዓመት ያደማን

ህሊና ቢስ ቡድን ቀን ተሌት ያጠቃን

ምኑ ያስገርማል ሰው ሰለቸኝ ብሎ ወደ አህያ ዞሮ

ትርፍ አመጣ ብሎ አህያ ቢበላ፡ ሀገርንም ቢሸጥ

ውርደትንም ለብሶ

ቢያሻሽጥ አህያ ዋጋ ያውጣል ብሎ ?